## ምርመራ ማን ማድረግ አለበት?



- በተላላፊ ሳንባ ነቀርሳ (ቲቢ) ከተያዘ ሰው ጋር **ግንኙነት** የነበረው ሰው።
- በእለታዊ እንቅስቃሴያቸው ፣ አኗኗር፣ ስራ ለሳንባ ነቀርሳ (ቲቢ) **ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች**።

## ምን አይነት ህክምና ያስፈልጋል?

የሳንባ ነቀርሳ በሽታ ምልክት ካለብዎ ሐኪሙ በሽታውን ለመከላከል ሚያስችል መድሃኒት ሊያዝ ይችላል። ሕክምናው በሽታ ለመፈወስ አይደለም፤ ምክንያቱም መደሃኒቱ በታዘዘሎት ወቅት አልታመሙም ። ወደፊት የህመም ምልክቶቹ ወደ ሳንባ ነቀርሳ (ቲቢ) በሽታ እንዳያድግ ለማድረግ ነው። በአጠቃላይ በየቀኑ አንድ መድኃኒት (አንቲባዮቲክ) ለ6 ወራት ያክል መውሰድ ይኖርቦታል።

የሳንባ ነቀርሳ ህመም መሆኑ ከተረጋገጠ
ራስን ከበሽታው ማዳን አስፈላጊ ነው። ሕክምናው ረጅም ነው ፣ ቢያንስ **ለ6ወራት** በየቀኑ በርካታ መድኃኒቶች(አንቲባዮቲክስ) መውሰድ ይጠይቃል። መድሃኒቱን በአግባቡ የወሰዱ እንደሆነ ፥ የመዳን እደልዎ መቶ በመቶ ይሆናል።



## ያነጋግሩን : አድራሻ

Fonds des Affections Respiratoires asbl

- **ማዕከላዊ ቡድን አድራሻ**
  Rue Haute, entrée 290 - 807A
  1000 Bruxelles
  **ስልክ**: 02 512 29 36 - Fax : 02 511 14 17
  prevention.tuberculose@fares.be

- **የብራሰልስ ሳንባ ነቀርሳ መከላከል ማዕከል**
  **ስልክ**: 02 511 54 01
  cpt.bruxelles@fares.be

- **የሄናውት ሳንባ ነቀርሳ መከላከል ማዕከል**
  **ስልክ**: 071 31 35 04
  cpt.hainaut@fares.be

- **የሊየጅ ሳንባ ነቀርሳ መከላከል ማዕከል**
  **ስልክ**.: 04 279 30 08
  cpt.liege@fares.be


- **የሉግዘምቡርግ ሳንባ ነቀርሳ መከላከል ማዕከል**
  **ስልክ**: 084 32 06 40
  cpt.luxembourg@fares.be

- **የናሙር እና ብራባንት ዋሉን ሳንባ ነቀርሳ መከላከል ማዕከል**
  **ስልክ**: 081 77 51 02
  cpt.namur-brabantwallon@fares.be

ለበለጠ መረጃ
**www.fares.be**

Responsible editor: Pr. Van Vooren, FARES asbl. D/2020/5052/1 Illustrations: Christian Papazoglakis

# ስለ ሳንባ ነቀርሳ ምን ያውቃሉ?



Amharic

## የሳንባ ነቀርሳ ምንድን ነው?

የሳንባ ነቀርሳ በሽታ በትንንሽ ህዋሳት (ጀርም) **ቲቢ ባሲሊከስ** ወይም ኮች ባሲሊከስ የሚመጣ ነው። የሳንባ ነቀርሳ በዋነኝነት ሳንባን ያጠቃል። እንዲሁም ሌሎች የሰውነት ክፍሎችን እንደ አጥንት፣ አንጀት፣ ኩላሊት እና አእምሮ ያጠቃል።

## በሳንባ ነቀርሳ ህመም ማን ሊጠቃ ይችላል?



ሳንባ ነቀርሳ **ተላላፊ** በሽታ ነው ።

የሳንባ ነቀርሳ (ቲቢ) ባሲለሶች በሳንባ ነቀርሳ በተጠቃ ሰው ሳንባ ውስጥ ይገኛሉ ። በበሽታው የተያዘ ሰው ሲያስል ፣ ሲያስነጥስ ወይም ሲናገር ጀርሞቹ አየር ላይ ይርቃሉ ። አንድ ሌላ ሰው ይህን አየር ወደ ውስጥ ቢስብ ጀርሞቹ በተመሳሳይ ጊዜ ይለቀቃሉ ።

ማንም ሰው በሳንባ ነቀርሳ አስተላላፊ ተህዋሳት (ቲቢ ባሲሊከስ) **ሊለከፍ (ሊያዝ)** ይችላል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ሰዎች ከሌሎች ይበልጥ በበሽታው የመያዝ እድላቸው ከፍተኛ ነው ። እንደ አኗኗር ሁኔታ እና እንደ ሥራ አይነት በሳንባ ነቀርሳ በሽታ ከተያዙ ሰዎች ጋር አዘውትረው የሚገናኙ ከሆነ በበሽታው የመያዝ እድልዎ ከፍተኛ ነው ።

## በድብቅ የሳንባ ነቀርሳ እና በንቁ የሳንባ ነቀርሳ ማካከል ያለ ልዩነት ምንድን ነው?



በሚተነፍሱበት ወቅት የሳንባ ነቀርሳ አምጪ ተህዋሳት (ቲቢ ባሲላይ) ወደ ሳንባ ዘልቀው ይገባሉ። በሰውነት ውስጥ ያለው መከላከያ አቅም፥ ህመም አምጪ ተህዋሳት ላይ ጥቃት የሚሰነዝሩ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ እነዚህን ተህዋሳት ያስወግዳል ። ተህዋሳቱ በሰውነት ውስጥ ከቀሩ አብዛኛውን ጊዜ ንቁ አይደሉም ወይም ጀርሞቹ ህይወት ቢኖራቸውም "ተኝተዋል"። ይህም ማለት አደገኛ አይደሉም ።የ **ድብቅ ሳንባ ነቀርሳ** በሽታ ካለብዎ ፤ ግን የህመም ምልክት ከሌለብዎ ፤ ለሌላ ሰው አያስተላልፉም።

በእድሜ የገፉ ከሆነ ፣ ወይም ልጅ ከሆኑ አልያም በሌሎች በሽታዎች የተዳከሙ ከሆነ ፣ በሰውነትዎ ውስጥ ያለው የመከላከያ አቅም ጀርሞችን (ተህዋሳትን) ለመዋጋት ደካማ ሊሆን ይችላል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ካጋጠመ "የተኙት" ሳንባ ነቀርሳ ተህዋሳት ሊነቃቁ ፣ ሊባዙና **የንቁ ሳንባ ነቀርሳ በሽታ** ሊያስከትሉ ይችላሉ ።

ሳንባን የሚያጠቃ የንቁ ሳንባ ነቀርሳ በሽታ ካለብዎ የሚከተሉትን ምልክቶች ሊያዩ ይችላሉ፥

- ሳል
- አክታ ያለው ሳል (አንዳንድ ጊዜ ደም የተቀላቀለበት)
- ድካም
- ትኩሳት
- ሌሊት ላብ
- ክብደት መቀነስ

**ከእነዚህ ምልክቶች መካከል አንዱ የሚሰቃዩ ከሆነ በተቻለ ፍጥነት ሐኪም ዘንድ ይሂዱ!**



ሳል



አክታ የተቀላቀለበት ሳል



ድካም



ትኩሳት



ሌሊት ላብ



ክብደት መቀነስ

## በሳንባ ነቀርሳ በሽታ በተያዘ ሰው የተጋለጡ ሰዎች፥ በበሽታው መያዛቸውን ወይም አለመያዛቸውን እንዴት ማወቅ ይቻላል?

ሐኪም በሳንባ ነቀርሳ ህማም አምጪ ተህዋስ መያዞን ወይም አለመያዞን ለማወቅ የሚያስችል **ቱበርክሊን** የተባለ በመርፌ የሚሰጥ ህክምና ያደርጋል። የህክምና ውጤት ከ3-5 ባሉት ቀናት ይደርሳል። ምርምራው **ቱበርክሊን የቆዳ ምርመራ** በመባል ይታወቃል ወይም በቀድሞ አጠራር ኢንትራደርማል ሪአክሽን ወይም ማንቶክስ ምርመራ በመባል ይታወቃል። የምርመራ ውጤቱ በጤና ባለሞያ መተርጎም (መገለጽ) አለበት።

ምርመራው ፖዘቲቭ (አዎንታዊ) ከሆነ የደረት ራጅ መነሳት አለበት:-

- የራጅ ውጤት የተለየ ነገር የማያሳይ ከሆነ **የድብቅ ሳንባ ነቀርሳ** አለብዎ ማለት ነው ።
- አለዚያ የ ንቁ ሳንባ ነቀርሳ መኖሩን ለማወቅ ተጨማሪ ምርመራዎች ያስፈልጋሉ ለምሳሌ:- ምራቅ ውስጥ ተላላፊ የሳንባ ነቀርሳ ህማም አምጪ ተህዋሳት መኖሩን መመርመር።